
EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 3

## ህንጻ እና የግንባታ ስራ

PK3



AppleTree

EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 3
## ህንጻ እና የግንባታ ስራ

AppleTree

©2020
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣ ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

**የቅጂ መብት** © 2020 **ጽሑፍ እና ስዕሎች።** AppleTree Institute(**አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት**) **መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።**

# PK3 ክፍል 3 አጠቃላይ እይታ



## ክፍል 3 ቃላት

- ረቂቅ ንድፍ
- ህንጻ
- የግንባታ ስራ
- የግንባታ ቦታ
- ስሜቶች
- እቅድ
- ሰማይ ጠቀስ ህንጻ
- መሳሪያ
- የእንጨት ስራ ቦታ

**ውድ ቤተሰቦች፣**

እንኳን ወደ ክፍል 3 ደህና መጣችሁ! ክፍል 3 የሚያወራው ስለ ህንጻ እና ህንጻ ስለመገንባት ነው! ልጆች ዕቅዶችን እና ንድፎችን ከማውጣት ጀምሮ እነሱን ወደሚታዩ ህንፃዎች እስከመቀየር ድረስ ያሉትን - የግንባታ ሂደቶች ይማራሉ።

## ክፍል 3 መጻህፍት




- ጎ አውሳይድ ኤንድ ፕሌይ/Go Outside and Play በ Felicia Truong
- የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/Mr. Star's New Home በ Mitchell Stevens
- ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears በ Felicia Truong
- ሼፕ ቢዩልደርስ/ Shape Builders በ Felicia Truong

***የ ECR @ Home ስራዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ ተገጣጣሚ ቅርጾችን መስራት፣ ስለ ስሜቶቻችን መደነስ፣ እስከ 3 ድረስ መቁጠር፣ ቅርጾችን መስራት፣ ስለ መሳሪያዎች ጨዋታ መጫወት፣ እና የቤተሰብ ቤት መገንባት።***


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሳምንት 1


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 አጠቃላይ እይታ

## ቤት መስራት/መገንባት



### በዚህ ሳምንት ውስጥ ልጅዎ፡

ቤት ለመስራት ስለሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች፣ ሠራተኞች እና ቁሳቁሶች ይማራል።

### ቁልፍ ቃላት



**ህንጻ**

ጣራ እና ግድግዳ ያለው እንደ ቤት ያለ ቦታ/ነገር



**የግንባታ ስራ**

እንደ ቤት እና መንገድ ያሉ ነገሮችን እንዴት እንደምንገነባ



**ስሜቶች**

እንደ ማዘን እና መደሰት ያሉ ስሜቶች


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስቡበት!

ይህ ሳምንት የሚያወራው ቤት ስለመገንባት ነው። ጥቅሉን ከመጀመርዎ በፊት፣ ምን አይነት ቤት ለመገንባት እንደሚፈልጉ ያስቡ። ሊገነቡት የሚፈልጉትን ቤት ስዕል ይሳሉ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ


PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 1

## STEM: መቁጠር እና መንቀሳቀስ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የተለያዩ የግንባታ ስራዎችን እንቅስቃሴዎች እያደረጋችሁ እስከ 3 መቁጠር ይለማመዱ። ይህንን ይበሉ፣ **እስኪ እስከ 3 ድረስ ቆጥረን በተለያዩ መንገዶች እንንቀሳቀስ! እንደ ቆፋሪ የምንቆፍር በመምሰል እስከ 3 ድረስ መቁጠር እንችላለን። 1, 2, 3! በጣም ግሩም የቁፈራ ስራ ነው!**
- እንደ ቀለም መቀባት፣ ንድፍ ማውጣት፣ ከባድ ጭነት ማራገፍ፣ ወዘተ ያሉ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ይሞክሩ። ልጅዎም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን መጠቆም ይችላል።

## በግል መማር: መስመሮች፣ ጥልፍልፎች እና ዙሮች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ ኮፒ ዘ ላየንስ/ Copy the Lines፣** ***በአማራጭነት - ጨው እና ሳህን***



- ልጅዎ የጽሑፍ መስመሮችን፣ ክቦችን እና ጥልፍልፎችን እንዲለማመድ ያበረታቱት።
- ልጅዎ የተጠማዘዘውን/ከርቭ መስመር በጣቱ ጥቂት ጊዜ **እንዲሰራ** ያድርጉት።
- ከዚያም፣ ልጅዎ ከለር በመጠቀም **እራሱን ችሎ መስመሮቹን መስራት** ይችላል።
- እርስዎ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ለመቅዳት እንድትችሉ ልጅዎ የራሱን ንድፍ መሳልም ይችላል!
- *በአማራጭነት - በሳህን ላይ ጨው ያስቀምጡ። በጨው ላይ እያንዳንዱን ንድፍ ለማስመሰል ልጅዎ ጣቱን እንዲጠቀም ያድርጉት።*


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 1

## ማንበብና መጻፍ: የኮኮብ ብርሃን/Star Light

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [የኮኮብ ብርሃን/Star Light]**





- ቅላጼ ያላቸውን ቃላት ማዳመጥን ይለማመዱ። **ቅላጼ ያላቸው ቃላት መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ ናቸው** ይበሉ። **አንድ ግጥም እናንብብ እና ቅላጼ ያላቸውን ቃላቶች እናዳምጥ።**
- አንድ ላይ ሆናችሁ ግጥሙን አንብቡ። ይህንን ይበሉ፣ መጨረሻቸው ላይ ተመሳሳይ የሆኑ አንዳንድ ቃላትን ሰምቻለሁ። **Light** እና **bright**።
- ግጥሙን ቀስ ብለው ያንብቡ። እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **የትኞቹን ቅላጼ ያላቸውን ቃላት ሰማህ?** tonight-might, light-bright)። ልጅዎ ቅላጼ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግር ከሆነ፣ ብዙም አይጨነቁ። አሁንም ገና እየተማረ ነው! ቃላቱን ለእሱ ይለዩለት።

## ያንብቡ: ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/*Go Outside and Play*


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [*ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play*]**


ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ





- አንድ ላይ ሆናችሁ፣ *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት* የሚለውን መጽሃፍ አንብቡ። ካነበባችሁ በኋላ ልጅዎ በመጽሐፉ ውስጥ የሚወደውን ገጽ እንዲመርጥ ያበረታቱት። እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **ይሄ ለምን የአንተ ተወዳጅ ገጽ ሆነ? በዚህ ገጽ ላይ ምን ዓይነት ቅርጾች ማየት ትችላለህ?**
- አብራችሁ ሆናችሁ፣ እነዚያን ቅርጾች በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ ለመፈለግ ሞክሩ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።







©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።







©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ኮከቧ ብርሃን፣ ኮኮቧ ደማቋ



ኮኮቧ ብርሃን ኮኮቧ ደማቅ ናት
ዛሬ ምሽቱ ላይ አንደኛ ያየኋት
ምነው ቢሆንልኝ ምነው ቢሆንልኝ
የእለቱን ምኞቴ ተሳክቶ ሞልቶልኝ




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 2

## STEM: የአየር ጥበብ/አርት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ውሀማ ቀለም (ቀለሙን በቀላሉ ለማንቀሳቀስ እንዲረዳ ተጨማሪ ውሃ) ወይም ምግብ ማቅለሚያ፣ ወረቀት**

- ይህንን ይበሉት፣ **በምንተነፍሰው አየር አርት/ጥበብ መስራት ትችላለህ።**
- በወረቀቱ ላይ ትንሽ ቀለም እንዴት ማድረግ እንዳሚቻል ለልጅዎ ያሳዩት፣ ከዚያም ቀለሙን ዙሪያውን ለማንቀሳቀስ ይተንፍሱ። አነስ ያለ እና ከባድ ትንፋሽ በመተንፈስ ልጅዎ እንዲመራመር ያበረታቱት።
- ከዚያ በኋላ እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **ስለሰራሀው የጥበብ ስራ ልትነግረኝ ትችላለህ? በቀስታ ስትተነፍስ ምን አስተዋልክ? እስትንፋስህን ስትቀይርስ ምን ተፈጠረ?**

## በግል መማር፡ የመገለል አይነት ስሜት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች ወይም ውሀማ ቀለም ጥቅሎች ከቀለም መቀቢያ ቡሩሽ ጋር**

- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ እንደተገለሉ ሆኖ ስለሚሰማዎት ጊዜ ይናገሩ። ይህንን ይበሉት፣ **አንዳንድ ጊዜ እንደተገለልን አይነት ሆኖ ይሰማናል። የተገለልክ አይነት ስሜት የተሰማህን ጊዜ ስዕል ሳል።**
- ከዛም በኋላ ይህንን ይበሉ፣ **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ። እንደተገለልክ አይነት ስሜት ሲሰማህ፣ ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ ለማድረግ ምን ማድረግ ትችላለህ?**


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ



## ማንበብና መጻፍ: ሀምፕቲ ዳምፕቲ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [ሀምፕቲ ዳምፕቲ/Humpty Dumpty]

- ዜማ/ቅላጼ ያላቸው ቃላትን ማዳመጥን ተለማመዱ። ልጅዎን **የዜማ ቃላት ድምጽ መጨረሻ ላይ አንድ አይነት ነው ለምሳሌ bat እና cat። እስኪ አሁን ግጥም እናንብብ እና ዜማ ያላቸው ቃላትን እናዳምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ግጥም ያንብቡ። **መጨረሻ ላይ አንድ አይነት ድምጽ ያላቸው ቃላትን አድምጫለሁ። ሀምፕቲና ዳምፕቲ** ብለው ይንገሩት።
- ግጥሙን በዝግታ ደግመው ያንብቡ። ከዚያም ልጅዎን **ምን አይነት የቃላት ዜማዎች አደመጥክ?** (wall-fall, men-again) ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ቅላጼ ያላቸውን ቃላትን ለመለየት የሚቸግር ከሆነ፣ ብዙም አይጨነቁ። አሁንም ገና እየተማረ ነው! ቃላቱን ለእሱ ይለዩለት።




## የጆርናል ሙከራ: የመገንቢያ አይነት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የመገንቢያ አይነት የጆርናል ገጽ**


- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ ስለ መገንቢያ/ገንቢ አይነቶች እና ሊገነቡ ስለሚችሉባቸው ቦታዎች ተነጋገሩ።
- ልጅዎ ስለሚሆነው የመገንቢያ አይነት ራሱን ችሎ እንዲስ እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- ከዚያ በኋላ እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **እንደዚህ አይነቱን መገንቢያ ለምን መረጥህ? እንደዚያኛው አይነት ገንቢ መሆን ምን ይመስልሃል?**




# ሃምፕቲ ዳምፕቲ

ሃምፕቲ ዳምፕቲ ሳት ኦን ኤ
ዋል።






ሃምፕቲ ዳምፕቲ ሃድ አ ግሬት ፎል።



ኦል ዘ ኪንግስ ሆርስስ
ኤንድ ኦል ዘ ኪንግስ ሜን፣



ኩድንት ፑት ሃምፕቲ ቱጌዘር አጌን።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________

ምን አይነት መገንቢያ መሆን ትፈልጋለህ?



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 3

## STEM: በመኖሪያ ቤት ዙሪያ የሚገኙ ቅርጾች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [ቅርጾች](#)፣ ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት**



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ቅርጾችን፡ ክብ፣ ሶስት ማዕዘን፣ ስኩዌር እና አራት ማዕዘን ይመልከቱ። ለልጅዎ ስለ ቅርጾች እና ስላሏቸው ጎኖች ብዛት ይንገሩት።
- ከዚያም **አሁን እነዚህን ቅርጾች የሚመስሉ ነገሮችን ለመፈለግ በመኖሪያ ቤታችን ዙሪያ እንዘዋወራለን** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ በመኖሪያ ቤትዎ ዙሪያ ቅርጹን የሚመስል ነገር ምሳ፡ ክብ የጣሳ ሊድ፣ አራት ማዕዘን የወለል ምንጣፍ፣ ወዘተ ለመፈለግ በምትዘዋወሩበት ወቅት ካርዶች ሊይዝ ይችላል።
- ቅርጾቹ ለክፍሉ ሌሎች ተግባሮች ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፡ መኖሪያ ቤትን ቀለም መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ውሀማ ቀለም ጥቅሎች ወይም ከለሮች፣ [የጂጂ ቤት/Gigi's House](#)**



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከስልክ ወይም ታብሌት ላይ የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች ስዕሎችን ይመልከቱ።
- ልጅዎን **መኖሪያ ቤት እንዴት መቀባት ትፈልጋለህ? ምን አይነት ቀለሞችን ትጠቀማለህ?** ብለው ይጠይቁት
- ከዚያም **ይህን ቤት በምትፈልገው መልኩ ቀለም መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መኖሪያ ቤት **ቀለም እንዲቀባ** ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 3

## ማንበብና መጻፍ፡ ስዕሎች እና ቃላት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ የትኛውንም ምስሎች ወይም ስዕሎች የያዘ መጽሀፍ**


- ለልጀዎ **መጻህፍት ስዕሎችና ቃላትን ይይዛሉ** ብለው ይንገሩት። ስዕሉን ያሳዩት እና **ይህ ስዕል ነው** ብለው ይንገሩት። ለቃላትም ተመሳሳዩን ደግመው ይስሩ።
- እስኪ **ገጽ ምረጥ እና በገጹ ላይ ያሉት ስዕሎች እና ቃላት የትኞቹ እንደሆኑ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።
- ተጨማሪ ገጾች ላይ ይህን ደግመው ይስሩ።

## ያንብቡ፡ ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/***Go Outside and Play***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት / Go Outside and Play*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Playን ያንብቡ።
- ቀጥለውም **አሁን በቤታችን ውስጥ የሚገኝ ቅርጽን ፈልገህ እንድታገኝ እጠራለሁ** ብለው ይንገሩት።
- የስራ ድርሻ ተቀያየሩ። ልጅዎን እርስዎ ፈልገው የሚያገኙት ቅርጽ ቆርጦ እንዲያወጣ ያድርጉ።

ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ



## እስኪ እንሂድ: ወደ ቅርጹ ይሂዱ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ቅርጾች ከቀዳሚው ተግባር ወደ ካርዶች ቆርጠው ያውጡ**



- ከወለሉ ጥቂት ጫማ አርቀው ቅርጾች ያስቀምጡ።
- **እስኪ እንደነገሩ ወደ ቅርጾቹ እንሂድ** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ቅርጽ ይጥሩና እንደ ወደ ክብ ቅርጽ መዝለል ወይም ወደ ስኩዌር ቅርጽ እየተወላገዱ መሄድ የመሳሰሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ይጠቁሙ።
- በተጨማሪም ልጅዎ እንደነገሩ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ቅርጾችን ሊጠቁም ይችላል።
- እነዚህን ቅርጾች በኋላ ላይ ለሚሰሩ ስራዎች ያስቀምጧቸው

## አንድ ላይ ሆኖ መማር: መኖሪያ ቤታችን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ እርሳሶች፣ ከለሮች**


- **እስኪ የመኖሪያ ቤታችንን ረቂቅ ንድፍ ወይም ዲዛይን እንስራ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ ስለሚገኙ ክፍሎች ይነጋገሩ እና ከዚያም አንድ ላይ ሆናችሁ የመኖሪያ ቤት ረቂቅ ንድፍ አዘጋጁና ቀለም ቀቡ።
- ከዚያም **ከመኖሪያ ቤታችን ውስጥ የምትወደው ክፍል የትኛው ነው? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 4


## **STEM:** ጠንካራው የትኛው ነው?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ወረቀት፣ እርሳሶች፣ መጽሀፎች የመሳሰሉ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች፣ *በአማራጭነት* - አየር ማስገቢያ ወይም ፀጉር ማድረቂያ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው አንድን ህንጻ ንፋስ በሚነፍስበትም ጊዜ ጭምር ጠንክሮ እንዲቆይ ስለሚያደርጉት ስለተለያዩ አይነት የህንጻ መሳሪያዎች ተነጋገሩ።
- ከዚያም **እስኪ አሁን ንፋስ በምናናፍስበት ወቅት የትኞቹ ነገሮች እንደሚንቀሳቀሱ እንመልከት** ብለው ይንገሩት። በተለያዩ ቁሶች ላይ አየር ያናፍሱ። በተጨማሪም የአየር ማስገቢያ ወይም ፀጉር ማድረቂያ በአማራጭነት ልትጠቀሙ ትችለላችሁ።
- ቀጥለውም **አየር በምናናፍስበት ወቅት ይሄኛው ነገር ለምን እንደተንቀሳቀሰ እና ይሄኛው ለምን አልተንቀሳቀሰም ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር፡ ቅርጾችን መለየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [ቅርጾች](#) ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት**



- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እያንዳንዱን ቅርጽ በስም ይጥሩ
- ለልጅዎ **ተመሳሳይ ቅርጾችን አንድ ላይ በማድረግ ቅርጾችን ለይ** ብለው ይንገሩት። ለምሳሌ ያክል አንድ ቅርጽ አብረውት ይለዩ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን 4

## ማንበብና መጻፍ፡ እኔን ተከተለኝ

- ልጀዎን **እስኪ አሁን እኔን ተከተለኝ ጨዋታ እንጫወት። የምለውን አድምጠኝ እና ከዚያም አድርግ** ብለው ይንገሩት።
- እንደ መዝለል፣ ጣቶችን መጨበጥ፣ መወላገድ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት።
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያዎች መስጠት እንዲችል የስራ ድርሻ ተቀያየሩ።

## የጆርናል ሙከራ: የግንባታ ተሽከርካሪዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የግንባታ ተሽከርካሪዎች የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ ግንባታ ተሽከርካሪዎች አይነቶች እና አገልግሎቶቻቸው ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለሚወደው የግንባታ ተሽከርካሪ አይነት ንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ይህን የግንባታ ተሽከርካሪ አይነት ለምን መረጥከው? ይህን የግንባታ ተሽከርካሪ ማሽከርከር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።


ስም:________________

ስለምትወደው አይነት የግንባታ ተሽከርካሪ ስዕል ስራ እንዲሁም ጽሁፍ ጻፍ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:_________________

ስለምትወደው አይነት የግንባታ ተሽከርካሪ ስዕል ስራ እንዲሁም ጽሁፍ ጽፍ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# አርብ



## STEM: የቅርጽ ስም መጥራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ቅርጾች ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት**

- ከልጅዎ ጋር ሆነው የእያንዳንዱን ቅርጽ ስም ይጥሩ።
- ከዚያም **አሁን ፍንጭ እሰጥህና አንተ የቅርጹን አይነት ትገምታለህ** ብለው ይንገሩት።
- እንደ **ይህ ቅርጽ 4 እኩል ማዕዘኖች አሉት** የመሳሰሉ ፍንጮች ይስጡት። ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገው እንኳ ምንም ማለት አይደለም። አሁንም ገና እየተማረ ነው!
- ልጅዎ ለእርስዎ ፍንጭ መስጠት እንዲችል የስራ ድርሻ ተቀያየሩ።



## በግል መማር: የቅንጣትሴና መንካት ኮሌጅ/Texture and Touch Collage

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ የተለያዩ ቅንጣቶች/ልስላሴዎች ያላቸው እንደ ብርጭቆ፣ ትንሽ ጠጠሮች እና ስፖንጅ የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንደ ለስላሳ ጨርቆች ወይም ሻካራ ምንጣፍ የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ልስላሴዎች ያላቸው ቁሶችን ልስላሴ በመንካት ለማወቅ ይሂዱ።
- ለልጅዎ **እነዚህን ነገሮች በወረቀት ላይ በማጣበቂያ በማጣበቅ የልስላሴ ኮሌጅ መስራት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ኮሌጅ እንስራ ያድርጉ።
- ከዚያም **እነዚህ ነገሮች ምን አይነት ስሜት ይሰጡሀል?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# አርብ



## ማንበብና መጻፍ፡ ስለ ገጽ መግለጽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/Go Outside and Play***

- ለልጅዎ **ገጽ ምረጥ እና በገጹ ላይ ምን እንደሚከናወን ግለጽልኝ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን **ምን አይነት ቅርጾች ይታዩሀል?** ወይም **ምን ይታይሀል?** የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊመሩት ይችላሉ።




## ያንብቡ፡ *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት*/***Go Outside and Play***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/ Go Outside and Play***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወት/ Go Outside and Play* ን ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ልጅዎን በዙሪያው ስለሚገኙ ቅርጾች ፍንጭ ይስጡት እና ቁሱን መገመት ይችል እንደሆነ ይመልከቱ። ለምሳሌ **ጊዜን የሚነግረኝ ክብ የመሰለ ነገር ይታየኛል** ብለው ሊነግሩት ይችላሉ።

ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሳምንት 2


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 አጠቃላይ እይታ


## ረቂቅ ንድፎች እና የግንባታ ሰራተኞች

### በዚህ ሳምንት ውስጥ ልጅዎ:

ስለ ረቂቅ ንድፎችና እና በግንባታ ቦታ ስለሚሰሩ የግንባታ ሰራተኞች አይነት ይማራል።



### ቁልፍ ቃላት



**ረቂቅ ንድፍ**

በወረቀት ላይ የሚሳል የህንጻ ፕላን



**የግንባታ ቦታ**

የተወሰነ የግንባታ ስራ የሚሰራበት ቦታ



**እቅድ**

የተወሰነ ነገር የሚሰራበት ዘዴ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስቡበት!

ይህ ሳምንት ስለ ረቂቅ ንድፍ እና ግንባታ ስራ የምንማርበት ነው። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ስለ ግንባታ ቦታ ይሳሉ እንዲሁም ይጻፉ



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 6

## **STEM:** ቅርጽ መለየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [ቅርጾች/Shapes]() ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት**



- የተለያዩ ቅርጾችን በስም ይጥሩ።
- ለልጅዎ **ተመሳሳይ የሆኑ 2 ቅርጾች ፈልግና አንድ ላይ አድርጋቸው** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ሌሎች ቅርጾችን እንዲለይ ያድርጉ።
- ቅርጾቹን በዚህ ሳምንት ለሚሰሩ ሌሎች ስራዎች ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር: ህንጻ ቀለም መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በመስኮት ውጭ ስለሚታዩዋችሁ ህንጻዎች ግለጹ ወይም ከስልክዎ፣ ታብሌት ወይም መጽሀፍ ላይ የህንጻ ስዕሎችን ተመልከቱ።
- ለልጅዎ **የትኛውንም የምትፈልገውን ህንጻ ቀለም መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ህንጻ ቀለም እንቀባ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ህንጻህ ንገረኝ። የትኛውም ቅርጾች ይታዩሀል?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 6

## ማንበብና መጻፍ: የአካል ክፍሎች

- ለልጅዎ **እስኪ እንጫወት፣ አንተ እኔን ተከተለኝ። የምናገረውን ነገር አዳምጥና አድርግ** ብለው ይንገሩት።
- **አፍንጫህን ጠቁመህ አሳየኝ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ እንደ ጆሮህን ንካ፣ እጅህን ንካ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት።
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያዎችን መስጠት እንዲችል ሚና ተቀያየሩ።

## ያንብቡ: የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/*Mr. Star's New Home*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [*የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home*]

- *የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home*ን አንድ ላይ ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ከገጽ 8 እስከ 15 መካከል ገጽ ይምረጡ። ከዚያም **ይህ ማሽን ምን ይሰራል? ስሙን ታስታውሰዋለህ?** ብለው ይጠይቁት።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ




## STEM: ፕላን ማዘጋጀት እችላለሁ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ እርሳስ ወይም ከለሮች፣ እንደ የፕላስቲክ መያዣዎች ወይም ሳጥኖች የመሳሰሉ ንጹህ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ *በአማራጭነት - ብሎኬቶች***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የቤት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ፕላን ማዘጋጀት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ይነጋገሩ። ከዚያም **የግንባታ ሰራተኞች ግንባታ ከመጀመራቸው በፊት ምን እንደሚሰሩ ለማወቅ እንዲያስችላቸው ፕላን ወይም ረቂቅ ንድፍ ማዘጋጀት አለባቸው** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን በእቃ መያዣዎቹ መስራት ለሚችለው የተወሰነ ነገር እራሱን ችሎ ፕላን እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ፕላኑ ለመገንባት እንዴት ይረዳሀል?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር: ቅርጾችን መሳል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ቅርጾች ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት፣ ወረቀት፣ ከለሮች**



- ልጅዎን እያንዳንዱን ቅርጾች በስም እንዲጠራ፣ ጎኖቻቸውን እንዲቆጥር እና የቅርጾቹን አቀማመጥ በጣቱ ጠቁሞ እንዲያገኝ ያድርጉ። ከዚያም **ይህ ስኩዌር ነው። እስኪ ጎኖቹን እንቁጠር 1፣ 2፣ 3፣ 4። 4 ጎኖች አሉት** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ቅርጾችን እንዲስል ያድርጉ። ቅርጾቹን በትክክል ባይስልም ይህ ምንም ማለት አይደለም። ገና እየተማረ ነው!
- ቅርጾቹን በዚህ ሳምንት ለሚሰሩ ሌሎች ስራዎች ያስቀምጧቸው።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 7

## ማንበብና መጻፍ፡ አናጺዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ አናጺዎች**

- የቃላትን የግጥም ምት ማዳመጥን ተለማመዱ። ለልጅዎ **ምት ያላቸው ቃላት መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ ድምጽ አላቸው፤ ለምሳሌ፡ jump እና bump። እስኪ ግጥም እያነበብን ተመሳሳይ ምት ያላቸው ቃላትን እናዳምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ግጥም ያንብቡ። ከዚያም **መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ቃላት ሰምቻለሁ፡ right እና height** ብለው ይንገሩት።
- ግጥሙን በዝግታ መልሰው ያንብቡ። ከዚያም **ምን ምት ያላቸው ቃላትን እየሰማህ ነው?** (right-height፤ might-sight) ብለው ይጠይቁት።



አናጺዎች

በ Cathryn O'Sullivan

አናጺዎች አንድን ቤት በትክክል ለመገንባት በርካታ ነገሮችን ይሰራሉ።

በመጀመሪያ፣ እንጨቱን ለቤቱ ቁመት ተስማሚ እንዲሆን አድርገው መቁረጥ አለባቸው።

ከዛ በኋላ፣ እንጨቱን በሚስማር በመዶሻ እና በሚችሉት ሁሉ ያያይዙታል።

በመጨረሻ፣ ቤቱን ቀለም ይቀቡታል። ዋው፣ እንዴት የሚያምር ቤት ነው!

## የጆርናል ሙከራ: የግንባታ ቦታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የግንባታ ቦታ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በግንባታ ቦታ ላይ ምን እንደሚከናወን ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ በግንባታ ቦታ ላይ ምን እንደሚሰራ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **በዚህ የግንባታ ቦታ ላይ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።



ስም:_________________

ስለ ግንባታ ቦታ ስዕል ሳል፣ እንዲሁም ጽሁፍ ጻፍ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# አናጺዎች

በ Cathryn O’Sullivan



አናጺዎች አንድን ቤት በትክክል ለመገንባት በርካታ ነገሮችን ይሰራሉ።

በመጀመሪያ፣ እንጨቱን ለቤቱ ቁመት ተስማሚ እንዲሆን አድርገው መቁረጥ አለባቸው።





ከዛ በኋላ፣ እንጨቱን በሚስማር በመዶሻ እና በሚችሉት ሁሉ ያያይዙታል።

በመጨረሻ፣ ቤቱን ቀለም ይቀቡታል። ዋው፣ እንዴት የሚያምር ቤት ነው!


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________

ስለ ግንባታ ቦታ ስዕል ሳል፣ እንዲሁም ጽሁፍ ጻፍ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 8

## STEM: እስከ 3 ድረስ በጣት መቁጠር

- ልጅዎን በጣቶች ስለመቁጠር ያስተምሩት። ከዚያም **እስኪ በጣቶቻችን እንቁጠር** ብለው ይንገሩት። በመጀመሪያ እርስዎ ያሳዩት እና **ምንም ጣት ከሌለ ዜሮ ማለት ነው** ብለው ይንገሩት።
    - **1 -** አውራ ጣትዎን ያንሱ
    - **2 -** አውራ ጣትዎን እና ጠቋሚ ጣትዎን አንድ ላይ ያንሱ
    - **3 -** ሶስቱን የመሀከል ጣቶችዎን ያንሱ
- ከዚያም **አሁን ደግሞ እኔ እቆጥራለሁ** ብለው ይንገሩት። አንድ ላይ ሆናችሁ ሁለት ጊዜ ጣቶቻችሁን ቁጠሩ።

## በግል መማር: ረቂቅ ንድፎች መሳል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ልጅዎን **ረቂቅ ንድፍ ምን እንደሆነ ታስታውሳለህ? አዎ ይህ የህንጻ ፕላን ወይም ዲዛይን ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **በቤት ውስጥ የሚገኝ ክፍል ረቂቅ ንድፍ ወይም ዲዛይን ማዘጋጀት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የመረጠውን ክፍል ረቂቅ ንድፍ እንዲስል ያድርጉ። የግድ በትክክል መሳል አይጠበቅበትም።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ረቂቅ ንድፍህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ



## ማንበብና መጻፍ፡ ይህን ሞክረው

- ለልጅዎ **እስኪ ይህን ሞክረው ጨዋታ እንጫወት። እኔ የምነግርህን ነገር አድመጥ። ከዚያም ያልኩትን ማድረግ ወይም ማስመሰል ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- **ፀጉርህን አሻሽ** ይበሉት።
- ልጅዎን የተወሰነ ነገር እንዲያደርግ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያ ይስጡት፤ ምሳ፡ ጥርስህን ቦርሽ፣ አይኖችህን አርገብግብ፣ ወደ ዋና ሂድ፣ ወዘተ።
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያ መስጠት እንዲችል ሚና ተቀያየሩ።

## ያንብቡ፡ የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/*Mr. Star's New Home*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home]*




- *የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home*ን አንድ ላይ ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ **ትንሹ ሊፍ ሎደር ሌሎቹ ማሽኖች ሊረዱት ባለመፈለጋቸው ምን ተሰማው? ትንሹ ሊፍን ጥሩ ስሜት እንዲፈጥርለት ለመርዳት ምን ትለዋለህ?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 8

## እስኪ እንንቀሳቀስ: እስከ 3 መቁጠር!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home]


- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የተለያዩ የግንባታ እንቅስቃሴዎችን እያደረጋችሁ እስከ 3 መቁጠር ይለማመዱ። **እስኪ እስከ 3 እንቁጠር እና በተለያዩ መንገዶች እንንቀሳቀስ! እንደ ትንሹ ሊፍ ሎደር አስመስለን እየተንቀሳቀስን እስከ 3 ድረስ መቁጠር እንችላለን። 1, 2, 3! በጥሩ ሁኔታ ጭነናል!** ብለው ይንገሩት።
- ከመጽሀፍ ላይ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ሞክሩ: ኬቲ ክሬን ማንሳት ወይም እንደ ብሩኖ ቡልዶዘር መስራት። ልጅዎም እንቅስቃሴዎችን ሊጠቀም ይችላል።



## አንድ ላይ ሆኖ መማር፡ ክቦችን፣ ሶስት ማዕዘኖችን እና 4 ማዕዘኖችን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [ቅርጾች፣] **ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት፣ የመጫወቻ ሊጥ ወይም እንደ ከለሮች፣ ክር ወይም የጥጥ ድር የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እያንዳንዱን ቅርጽ በስም ይጥሩ (ዳይመንድ፣ ክብ፣ አራት ማዕዘን)፤ ጎኖቻቸውን ይቁጠሩ እንዲሁም ልጅዎን የቅርቶቹን ርእስ በጣቱ ጠቁሞ እንዲያመለክት ያድርጉ። **ይህ አራት ማዕዘን ነው። እስኪ ጎኖቹን 1, 2, 3, 4.። 4 ጎኖች አሉት** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን የመጫወቻ ሊጥ ወይም ሌሎች ቁሳቁሶችን በመጠቀም እራሱን ችሎ ቅርጾችን እንዲሰራ ያድርጉት።
- ቀጥለውም **ጎኖች የሌሉት የትኛው ቅርጽ ነው?** ብለው ይጠይቁትና **አዎ፣ ክብ ነው** ብለው ይንገሩት።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 9


## **STEM:** መገንባት እችላለሁ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ የጭማቂ ሳጥኖች ወይም የፕላስቲክ መያዣዎች የመሳሰሉ ንጹህ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **የተወሰነ ነገር እገነባለሁ/ እሰራለሁ ከዚያም ይህን ነገር መልሰህ አንተ እንድትሰራው እፈልጋለሁ** ብለው ይንገሩት።
- የተወሰነ ቀላል ነገር ይስሩ እና የሰሩትን ነገር ይግለጹለት። ለልጅዎ **ይህን ከሌላኛው በላይ አስቀምጠዋለሁ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የተወሰነ ነገር በመቅዳት እንዲገነባ ያድርጉት። ልጅዎ የተለየ ነገር ለመገንባት ከፈለገ ይህም ጥሩ ነው።
- እርዳታ ቢጠይቅዎም ይህም ምንም ማለት አይደለም፣ ፍንጭ ሊሰጡት ወይም አብረውት ሊገነቡ ይችላሉ።
- ከዚያም ሚና ተቀያየሩ፣ ልጅዎ እርስዎ የሚቀዱት የተወሰነ ነገር ሊገነባ ይችላል።

## በግል መማር፡ ህትመቶች መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ *ሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home*፣ ውህማ ቀለም ጥቅል ወይም ሌላ ቀለም፣ ወረቀት፣ እና እንደ ስፖንጅ፣ ዱንጋይ እና ቅጠል የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሰቁሶች**



- ለልጅዎ የሚ/ር ስታር ቤት/ *Mr. Star's Home* ገጽ.15ን ያሳዩት እና **ትንሿ ሊፍ ሎደር የማሽከርከሪያ መንገድ እየሰራች ነው። ሎደሯ ልዩ ዲዛይን አስቀምጣለች። አንተም እነዚህን ነገሮች የተለያዩ ዲዛይኖች ለመስራት ልትጠቀምበት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን አንድ ቁስ ቀለም ውስጥ እንዲጨምር እና ቁሱን ዲዛይን ለመስራት አውጥቶ ወረቀት ላይ እንዲጫነው ይንገሩት።
- ልጅዎን ቁሶችና ቀለም በመጠቀም እራሱን ችሎ ህትመቶች እንዲሰራ ያድርጉ።
- ከዚያም **ይህን ህትመት የሰራው የትኛው ቁስ ነው? ይህ ከዚህኛው የሚለየው እንዴት ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 9

## ማንበብና መጻፍ፡ ስዕሎች እና ቃላት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ የትኛውንም ምስሎች ወይም ስዕሎች የያዘ መጽሀፍ**

- ለልጀዎ **መጻህፍት ስዕሎችና ቃላትን ይይዛሉ** ብለው ይንገሩት።
- ስዕሉን ያሳዩት እና **ይህ ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። ለቃላትም ተመሳሳዩን ደግመው ይስሩ።
- እስኪ **ገጽ ምረጥ እና በገጹ ላይ ያሉት ስዕሎች እና ቃላት የትኞቹ እንደሆኑ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።
- ተጨማሪ ገጾች ላይ ይህን ደግመው ይስሩ።

## የጆርናል ሙከራ፡ አዲስ ከተማ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የአዲስ ከተማ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በአዲስ ከተማ ውስጥ መኖር ምን ይመስላል ብሎ እንደሚያስብ በተመለከተ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ በአዲስ ከተማ ውስጥ መኖር ምን ይመስላል ብሎ እንደሚያስብ እንደዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ምን እንደጻፍክና እንደሳልክ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


ስም:__________________

በአዲስ ከተማ ውስጥ መኖር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________________

በአዲስ ከተማ ውስጥ መኖር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# አርብ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን 10

## STEM: ቅርጽ ማስታወስ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [ቅርጾች](#) ከሳምንት 1 ቀን 3 ወስደው ወደ ካርዶች ቆርጠው ያውጧቸው**


- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው 3 ጥንድ ቅርጾችን ይምረጡ። ስም ይስጧቸው እና ከዚያም ገልብጠው ያስቀምጧቸው።
- ለልጅዎ **ማዛመድ እና ተመሳሳይ የሆነ ቅርጽ ማግኘት ትችል እንደሆነ ለማየት 2 ካርዶች ገልብጥ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ ማዛመድ ከቻለ ጥንድ ሊያነሳ ይችላል። ይህን ማድረግ ባይችልም ምንም ማለት አይደለም። ካርዶቹን መልሶ ገልብጦ በማስቀመጥ በድጋሚ ሊሞክር ይችላል።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ጌሙን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።



## በግል መማር: ቤቱን ማስዋብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: *[የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/ Mr. Star's New Home](#)*፣ ወረቀት፣ ከለሮች ወይም ውሀ ቀለም ጥቅል**

- ለልጅዎ ገጽ 20ን ያሳዩትና **የስታር ቤተሰብ ኮከቡን መኖሪያ ቤቱን በልዩ ሁኔታ ለማስዋብ ተጠቅሞበታል። አንተም የእኛን ቤት በልዩ ሁኔታ ልታስውብ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የማስዋብ ስራ እንዲሰራ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ እኛ ልዩ ማስዋቢያ ንገረኝ። ይህን ለእኛ ቤት የመረጥከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ማስዋቢያውን የሚያስቀምጥበት ልዩ ቦታ እንዲመርጥ ይፍቀዱለት።




©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# አርብ




## ማንበብና መጻፍ፡ የህንጻ መግለጫዎች

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በመኖሪያ መንደራችሁ በእግር ተዘዋወሩ ወይም በመስኮት በኩል ወደ ውጭ ተመልከቱ።
- ልጅዎን **ስላየሀቸው ህንጻዎች ልትገልጽልኝ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ተጨማሪ መረጃ እንዲያካትት ለመርዳት ተጨማሪ ጥያቄዎች ይጠይቁት፤ ለምሳሌ፡ **የህንጻው መጠን ምን ያክል ነው? ህንጻው ረጅም ነው ወይስ አጭር? ህንጻውን ለምን አገልግሎት ይጠቀሙበታል ብለህ ታስባለህ? ህንጻውን የገነቡት እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ?**

## ያንብቡ፡ የሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/***Mr. Star's New Home***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [*ሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/Mr. Star's New Home*]

- *ሚ/ር ስታር አዲስ ቤት/Mr. Star's New Home*ን ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ያንብቡ።
- ቀጥለውም **ቤት በምንገነባበት ወቅት ለምን የተለያዩ ማሽኖች ያስፈልጉናል?** ብለው ይጠይቁት።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሳምንት 3


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 አጠቃላይ እይታ

## የግንባታ መሳሪያዎች



### በዚህ ሳምንት ውስጥ ልጅዎ:

በህንጻ ግንባታ ቦታ ወይም ወርክሾፕ ቦታ ላይ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ስለተለያዩ የግንባታ መሳሪያዎች በተመለከተ ይማራል

### ቁልፍ ቃላት



**መሳሪያ**

የተወሰነ በእጅዎ የሚይዙትና ለስራዎ የሚጠቀሙበት መሳሪያ



**የዕንጨት ስራ ቦታ**

ነገሮችን መስራት ወይም መገንባት የሚችሉበት ቦታ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስቡበት!

የዚህ ሳምንት ትምህርት ስለ መሳሪያዎች የተመለከተ ነው። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት መሳሪያዎች ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ ያስቡ። ስለሚመርጡት መሳሪያ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ



## STEM: ቁሶችን መቁጠር


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: የጥጥ ኳሶች ወይም ማንኪያዎች የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**

- ልጅዎን **እስኪ በጋራ እንቁጠር** ብለው ይንገሩት።
- 3 ቁሶች ያስቀምጡና በሚቆጥሩበት ወቅት እያንዳንዱን ቁስ ይንኩ። ከዚያም **1, 2, 3። 3 ነገሮች አሉ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ከ1 እስከ 3 ቁሶች ያሳዩት እና እንዲቆጥራቸው ይንገሩት። ከዚያም **ሁሉም አንድ ላይ ስንት ናቸው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ ድምሩን ሳይናገር በድጋሚ የሚቆጥር ከሆነ እንዲረዳ ለማገዝ መጨረሻ ላይ የምትጠራው ቁጥር የቁሶቹን ጠቅላላ ድምር ይወክላል ብለው ሊነግሩት ይችላሉ። ምሳ: **2 ማንኪያዎች አሉ።**

## በግል መማር: መሳሪያዎችን ቀለም መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: መሳሪያዎችን ቀለም መቀቢያ ገጾች፣ ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ መሳሪያዎችና ለምን እንደሚያገለግሉ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መሳሪያዎችን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **የትኛውን መሳሪያ መጠቀም ትፈልጋለህ? ለምን?** ብለው ይጠይቁት።
- ስዕሎቹን በዚህ ሳምንት ለሚሰሩ ሌሎች ስራዎች ያስቀምጧቸው።




መዶሻ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 11


## ማንበብና መጻፍ፡ ገጽ መግለጥ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ የትኛውም መጽሀፍ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው መጽሀፍ እንዴት እንደሚያዝና ገጽ እንዴት እንደሚገለጥ ይንገሩት። ከዚያም **መጽሀፍ የምንይዘው የፊት ሽፋኑን ለማየት እንዲያስችለን የቀኝ ጎኑን ወደ ላይ አድርገን ነው** ብለው ይንገሩት። የፊት ሽፋኑን ጠቁመው ያሳዩት። **ከዚያም እያንዳንዱን ገጽ ለማንበብ በጥንቃቄ እንገልጠዋለን** ብለው ይንገሩት። የመጽሀፍ አያያዝ እና ገጽ አገላለጥ ምሳሌ ያሳዩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የመጽሀፍ የፊት ሽፋን እንዲያሳዩዎትና የተወሰኑ ገጾቹን እንዲገልጥ ያድርጉ።


## ያንብቡ፡ ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/ ***Just Right: Lou Lou and the Bears***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** [ስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears](#), ***በአማራጭነት- የሙቀት መጠን መለኪያ***




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *Just Right: Lou Lou and the Bears* መጽሀፍን ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ስለ የሙቀት መለኪያ ይንገሩት። **የሙቀት መለኪያ የሆነ ነገር ምን ያክል ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ እንደሆነ ለማየት የሙቀት መጠን ለመለካት ይረዳናል። የሰውነታችንን፣ የምግብ ወይም የአየር የሙቀት መጠን መለካት እንችላለን። Lou Lou ከአጃ የተዘጋጀ ምግብ የሙቀት መጠን ለመለካት የተጠቀመው የምግብ የሙቀት መጠን መለኪያ ነው** ብለው ይንገሩት እና **የአጃ ምግቡ በጣም ሞቃት ቢሆን ምን ሊሆን ይችላል?** ብለው ይጠይቁት
- *በአማራጭነት:* በተጨማሪም የሙቀት መለኪያ በመጠቀም እርስ በርሳችሁ ሙቀታችሁን ልትለካኩ ትችላላችሁ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።



# መዶሻ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።



መፍቻ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 12

## STEM: የህንጻ ጥንካሬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ የሶፍት መጠቅለያ፣ አነስተኛ የፕላስቲክ መያዣዎች የመሳሰሉ በድጋሚ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ላይ ሆነን የተወሰነ ነገር እንገንባ። ከዚያም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ እንመልከት** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በድጋሚ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በወረቀት ጫፍ ላይ መዋቅር ይገንቡ።
- ከዚያ በኋላ ልጅዎን መዋቅሩ የሚወድቅ ስለመሆኑ ለማየት ወረቀቱን ቀስ ብሎ ወደፊትና ወደ ኋላ እንዲስበው ይፍቀዱለት። ከዚያም ልጅዎን መዋቅሩን ለመጣል ምን ያክል በፍጥነት መሳብ እንደሚችል እንዲያውቅ ወረቁቱን በፍጥነት እንዲስበው ያድርጉ።
- ከዚያም **ህንጻችንን ለመጣል ወረቀቱን ምን ያክል በፍጥነት ልትስበው ትችላለህ? ህንጻው ወረቀቱን በዝግታ ስትስበው ያልወደቀው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።

## በግል መማር: የእንጨት ስራ ኮሌጅ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ *በአማራጭነት - ማጣበቂያ፣ ከመጽሄት ወይም በራሪ ጽሁፎች የተወሰዱ ስዕሎች***

- ከልጅዎ ጋር በቤተ ሙከራው መጠቀም ስለሚፈልጋቸው ስለተለያዩ መሳሪያዎች ተነጋገሩ።
- **ኮሌጅህን በምትፈልጋቸው መሳሪያዎች ልትሰራ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መሳሪያዎቹን በመሳል ወይም ስዕሎቹን በማጣበቅ ኮሌጁን እንዲሰራ ያድርጉት።
- ከዚያም **ለኮሌጅህ እነዚህን መሳሪያዎች የመረጥካቸው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ



## ማንበብና መጻፍ: ስለ መሳሪያ መግለጽ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: መሳሪያዎችን መቀቢያ ገጾች፣ የመሳሪያዎች ስዕሎች ወይም እውነተኛ መሳሪያዎች**




- ልጅዎን **እስኪ ስለ እነዚህ መሳሪያዎች እንግለጽ** ብለው ይንገሩት። ስለ መሳሪያዎቹ አንድ ላይ ሆናችሁ ግለጹ። ስለ መሳሪያዎቹ ቀለም፣ መጠን፣ ቅርጽ፣ እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ልትነጋገሩ ትችላላችሁ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለ ሌላ መሳሪያ እንዲገልጽ ያድርጉ።
- ልጅዎን ስለመሳሪያው እንዲገልጽ ለመርዳት ጥያቄዎች ይጠይቁት። **ይህን መሳሪያ እንዴት እንጠቀምበታለን? መሳሪያው መጠኑ ትልቅ ነው ወይስ ትንሽ? መሳሪያው ከባድ ነው ወይስ ቀላል?**

## የጆርናል ሙከራ: መሳሪያዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የመሳሪያዎች የጆርናል ገጽ**


ስም:_________________

ለመሞከር የምትፈልገው የትኛውን መሳሪያ ነው?

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለሚመርጠው መሳሪያ ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መጠቀም ስለሚፈልገው መሳሪያ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **የመረጥከው የትኛውን መሳሪያ ነው? ይህን መጠቀም የፈለከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________

ለመሞከር የምትፈልገው የትኛውን መሳሪያ ነው?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# ረቡዕ



## STEM: ነጥቦችን መቁጠር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [ከ0-3 የነጥብ ካርዶች], ከለሮች፣ እንደ የወረቀት ማጣበቂያዎች ወይም ትናንሽ ጠጠሮች የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች**


- ለልጅዎ **እስኪ በእያንዳንዱ ካርድ ላይ የሚገኙትን ነጥቦች እንቁጠር** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን እያንዳንዱን ነጥቦች በሚቆጥርበት ወቅት በጣቱ እንዲነካ ይርዱት። የመጨረሻውን የቆጠራ ውጤት ይድገሙ። **አንድ፣ ሁለት። ሁለት ነጥቦች አሉ** ይበሉ።
- ልጅዎን **እስኪ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው የወረቀት ማጣበቂያዎች በነጥቦቹ ላይ እናድርግ** ብለው ይንገሩት። በሚቆጥሩበት ወቅት የወረቀት ማጣበቂያዎቹን በነጥቦቹ ጫፍ በማስቀመጥ ምሳሌ ይስጡት። **የወረቀት ማጣበቂያዎቹን ከነጥቦቹ ጋር የማዋድደው እየቆጠርኩ ነው** ይበሉት። **አንድ** (የመጀመሪያውን የወረቀት ማጣበቂያ የመጀመሪያው ነጥብ ላይ ያድርጉ)፣ **ሁለት!** እያሉ ይቀጥሉ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ በሌሎች 2 ካርዶች እንዲሰራ ያድርጉት።



## በግል መማር: የህንጻ ዝግጅቶች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: [የህንጻ አቀማመጦች], ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ህንጻ ዝግጅቶች ተነጋገሩ። **የግንባታ ሰራተኞች በመጀመሪያ የህንጻውን ረቂቅ ንድፍ ወይም ፕላን ያዘጋጃሉ፤ ቀጥለውም ህንጻው የሚሰራበትን መሬት ያጸዳሉ። ከዚያም የሚያስፈልጓቸው ሁሉንም መሳሪያዎች አንድ ላይ ያሰባስባሉ። በመጨረሻም በተጸዳው መሬት ላይ ህንጻውን መገንባት ይጀምራሉ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ እያንዳንዱን ስዕል ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም ልጅዎ እራሱን ችሎ ቅደም ተከተሎቹን ሊያስቀምጥ ይችላል።
- ቀጥላችሁም ደረጃዎቹን በጋራ ስሩ። **መጀመሪያ የሚመጣው የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።


# ረቡዕ



## ማንበብና መጻፍ: ዝናብ፣ ዝናብ/ **Rain, Rain**

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [ዝናብ፣ ዝናብ/ Rain, Rain]


- የቃላት ምትን ማዳመጥ ተለማመዱ። **ምት ያላቸው ቃላት መጨረሻው በተመሳሳይ ድምጽ ያበቃል: fish እና wish። እስኪ ግጥም እናንብብ እና ምርት ያላቸው ቃላትን እናድምጥ** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ላይ ግጥሙን ያንብቡ። **መጨረሻ ላይ አንድ አይነት ድምጽ ያላቸው ቃላት ሰምቻለሁ: day እና play** ብለው ይንገሩት።
- በዝግታ ግጥሙን ደግማችሁ አንብቡ። **ምን ምት ያላቸው ቃላትን አድምጠሀል?** (day, away, እና play) ብለው ይጠይቁት።




## ያንብቡ፡ ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/ ***Just Right: Lou Lou and the Bears***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *[ጀስት ራይት: ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears]*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *ጀስት ራይት: ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears* ን አንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ህጻኑ ድብ ምን አይነት ስሜት እንደተሰማው በጋራ ተነጋገሩ። **ህጻኑ ድብ ወንበሩ በጭቃ ተለውሶ ሲያገኘው እና ምንም የቀረ የአጃ ምግብ ሲያጣ ምን አይነት ስሜት ተሰምቶት ነበር ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- **Lou Lou የአጃ ምግቡን በመብላቱና ወንበሩ ላይ በመቀመጡ ደስተኛ የሆነ ይመስላል። ሆኖም ህጻኑ ድብ በጣም አዝኗል። Lou Lou ህጻኑን ድብ ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላል?** ብለው ይጠይቁት።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 13

## እስኪ እንንቀሳቀስ: ቁም! ተራመድ/ሂድ!


- ከልጅዎ በተወሰነ ጫማ ርቀት ይቁሙ። **እስኪ በግንባታ ቦታና በመኖሪያ መንደራችን እንዴት ደህንነታችንን እንደምንጠብቅ እንለማመድ። እስኪ ቁም! ሂድ/ተራመድ! ጨዋታ እንጫወት** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እኔ "ሂድ" ስልህ ትሄዳለህ። እኔ ‹‹ቁም›› ስልህ ትቆማለህ። መሄድ ሳይኖርብህ የምትሄድ ከሆነ ወደ ኋላ መመለስ አለብህ** ብለው ይንገሩት።
- አንድ ዙር ተጫወቱ። ልጅዎ መቼ መቆም ወይም መሄድ እንዳለብዎ እንዲነግርዎ ሚና ተቀያየሩ።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፡ ምን ስሜት ይሰማሀል?


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **እስኪ አሁን ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማን እንሳል** ብለው ይነገሩት።
- የተለያዩ ስዕሎችን ሳሉ። ከዚያም ስለ ስዕሎቻችሁና ስሜቶች ተነጋገሩ።
- ከዚያም **አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ተመሳሳይ ስሜቶች ሊኖሯቸው እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የተለያዩ ስሜቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። እኔ የደስታ ስሜት እና አንተ ደግሞ የመረጋጋት ስሜት ሊኖርህ ይችላል። የተለያየ ስሜት ቢሰማንም ምንም ማለት አይደለም!** ብለው ይንገሩት።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።





ረቂቅ ንድፉን ይሳሉ



ቁሳቁሳቁሶቹን ሰብስቡ




የግንባታ መሬቱን አጽዱ



በግንባታ ቦታው መስራት


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሬይን ሬይን



ሬይን ሬይን፣
ጎ አዌይ፣
ከም አጌን
አናዘር ዴይ።
ኦል ዘ ቺልድረን
ወንት ቶ ፕሌይ።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 14

## STEM: እስኪ እንለካ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: እንደ ወረቀት ማጣበቂያዎች፣ ከለሮች ወይም ማንኪያዎች የመሳሰሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **የግንባታ ሰራተኞች ለህንጻቸው የሚገጥሙ ነገሮችን ለማወቅ እንጨት ወይም ብረት ቆርጠው ለማውጣት ነገሮችን መለካት አለባቸው። እስኪ ስለ መለካት እንለማመድ** ብለው ይንገሩት።
- እንደ ከለሮች ወይም የወረቀት ማጣበቂያዎች የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም መለካት ተለማመዱ፤ ለምሳሌ: **እስኪ ምን ያክል ከለሮች የእጃችንን ያህል እንደሚረዝሙ እንለካ** ብለው ይንገሩት።

## በግል መማር: ለ ሉ ሉ የተጻፈ ደብዳቤ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** [*ጀስት ራይት: ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears*]

- ልጅዎን **ህጻኑ ድብ ሉ ሉ/Lou Lou ገንፎውን ሲበላበት፣ ወንበሩ ላይ ሲቀመጥበትና መኝታው ላይ ሲተኛበት ምን አይነት ስሜት ተሰምቶታል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ **እንደ ህጻኑ ድብ ልታስመስል እና ለLou Lou ምን ስሜት እንደተሰማህ በተመለከተ ደብዳቤ ልትጽፍለት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ደብዳቤውን እንዲጽፍና እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ደብዳቤህ ንገረኝ። ለ Lou Lou ምን ብለህ ነገርከው?** ብለው ይጠይቁት።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 14

## ማንበብና መጻፍ፡ ስዕል ማንበብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ልጅዎ ከሚወዳቸው መጻህፍት መካከል አንዱ**

- ለልጅዎ **እስኪ ይህን በጋራ እንይ። ምን እንደተከሰተ ንገረኝ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን ገጾቹን በጥንቃቄ እንዲገልጥና በእያንዳንዱ ገጽ ላይ በሚገኙት ስዕሎች ላይ ምን እንደሚከሰት እንዲገልጽ ይርዱት።
- እንደ **ቀጥሎ ምን ይከሰታል ብለህ ታስባለህ? ለምን ይህን ልታስብ ቻልክ?** የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁት።

## የጆርናል ሙከራ፡ የእኔ የእንጨት ስራ ቦታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የእኔ ቤት ሙከራ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የምናብ የእንጨት ስራ ቦታው ምን ሊመስል እንደሚችል በተመለከተ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን የእንጨት ስራ ቦታ ቢኖረው ምን ሊሰራ እንደሚችል እራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **የእንጨት ስራ ቦታ ቢኖርህ ምን ታደርጋለህ? ለምን ይህን መስራት መረጥክ?** ብለው ይጠይቁት።


ስም:_________________

የእንጨት ስራ ቦታ ቢሆርህ፣ ምን ትሰራ ነበር?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________

የእንጨት ስራ ቦታ ቢሆርህ፣ ምን ትሰራ ነበር?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# አርብ



## STEM: 3ን ማግኘት!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች**

- ልጅዎን **እስኪ ጌም እንጫወት። እኔ አንድ ቁስ እና ቁጥር እጠራ እና አንተ ደግሞ በቤት ውስጥ የሚገኙ መልሰን ማምጣት የምንችላቸው ብዙ ቁሶችን እንድትፈልግ እፈልጋለሁ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን በቤት ዙሪያ ከ1 እስከ 3 ቁሶችን እንዲፈልግ ይጠይቁት። ለምሳሌ: **3 ማንኪያዎችን ፈልግ።** ልጅዎ የተጠየቀውን ያህል ቁጥር ባያመጣም ምንም ማለት አይደለም። ቁሶቹን ጠቁመው እያሳዩ እያንዳንቸውን ይቁጠሩ። **1፣ 2፣ 3። ሶስት ማንኪያዎች አሉ።**
- ልጅዎ ምን ያክል ቁሶች እንደሚፈልጉ እንዲነግርዎ ሚና ተቀያየሩ።

## በግል መማር: የእኔ ልዩ መሳሪያ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች፣ *በአማራጭነት* - ማጣበቂያ፣ በቤት ውስጥ የሚገኙ ህንጻ ለመስራት የሚያገለግሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ ምሳሌ: ትናንሽ የፕላስቲክ መያዣዎች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ መሳሪያዎች ይነጋገሩ።
- **መሳሪያ መስራት ብትችል ምን አይነት መሳሪያ ትሰራለህ? መሳሪያው ለምን ያገለግላል?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን እራሱን የሱን ልዩ መሳሪያ ዲዛይን እንዲያዘጋጅና እንዲስል ያድርጉ። ልጅዎ መሳሪያውን በአማራጭነት በቤት ውስጥ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ሊሰራ ይችላል።
- ቀጥለውም **ስለ መሳሪያህ ልትነግረኝ ትችላለህ? መሳሪያው ምን ይባላል? ለምን ያገለግላል?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# አርብ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን 15

## ማንበብና መጻፍ፡ ስለ መጽሀፍ ገጽ መግለጽ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears***



- ለልጅዎ **ገጽ ምረጥና በገጹ ላይ ምን እነደሚከሰት ግለጽ** ብለው ይንገሩት።
- እንደ **ድቦቹ ምን ይሰማቸዋል ብለህ ታስባለህ? ይህን እንዴት መናገር ትችላለህ?** የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ልጅዎን በመምራት ሊያግዙት ይችላሉ።


## ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ: ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/ ***Just Right: Lou Lou and the Bears***

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ***ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears*፣ *በአማራጭነት - መለኪያ ሜትር ወይም ማስመሪያ***




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *ጀስት ራይት፡ ሉ ሉ እና ዘ ቤርስ/Just Right: Lou Lou and the Bears* ን ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ በጋራ ስለ መለኪያ ሜትር ተነጋገሩ። **የመለኪያ ሜትርን የተወሰነ ነገር ርዝመቱ፣ ስፋቱ ወይም ቁመቱ ምን ያክል እንደሆነ ለመለካት እንጠቀምበታለን። የግንባታ ሰራተኞች እንደ እንጨት ያሉ ነገሮችን ከመቁረጣቸው በፊት ለመለካት ይጠቀሙበታል። በተጨማሪም የክፍል ስፋት ምን ያክል እንደሆነ ይለኩበታል። Lou Lou በመለኪያ ሜትሩ የሚለካበት ምን ነበር?**
- የመለኪያ ሜትር ወይም ማስመሪያ በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን መለካትን ልትለማመዱ ትችላላችሁ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።





©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሳምንት 4


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 አጠቃላይ እይታ

## የግንባታ ምልክ

### በዚህ ሳምንት ውስጥ ልጅዎ:

ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ይሰራል እንዲሁም ስለ መሳሪያዎች መማሩን ይቀጥላል።



### ቁልፍ ቃላት



## ሰማይ ጠቀስ

ሰማይ ጠቀስ: ሰማይ ጠቀስ የህንጻ ቅርጽ ነው



## መሳሪያ

በእጅዎ የሚይዙትና ስራዎን ለመስራት የሚጠቀሙበት ነገር


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስቡበት!

በዚህ ሳምንት ስለ ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ወይም ህንጻዎች ሰማይ ላይ ስለሚሰሩት ቅርጽ ትማራላችሁ። መርሀግብሩን ከመጀመርዎ በፊት በመስኮት ወደ ውጭ ይመልከቱ። ልጅዎን እስኪ ስላየኸው ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ንገረኝ። ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ሳል ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 16

## **STEM:** 1, 2, 3, ቁም

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** ***በአማራጭነት - ሙዚቃ***

- ለልጅዎ **እስኪ 1, 2, 3, ቁም የሚባለውን ጌም እንጫወት! እየደነስን እስከ 3 ድረስ እንቆጥራለን። 3 ላይ ስንደርስ እናቆምና ያለንበት ቦታ እንቆማለን። ከዚያም መደነሱን በድጋሚ ልንጀምር እንችላለን** ብለው ይንገሩት።
- በምትደንሱበት ወቅት ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ **1, 2, 3, ቁም!** እያላችሁ ቁጠሩ።
- *በአማራጭነት: ጌም እየተጫወታችሁ ሙዚቃ ተጫወቱ።*

## በግል መማር: ... ማድረግ ደስ ይለኛል

- ለልጅዎ **ይህ ስለ ግንባታ የምንማርበት የመጨረሻው ሳምንት ነው። ምን መማር ያስደስትሀል?** ብለው ይጠይቁት። መማር ስለሚያስደስትዎ ነገር ይግለጹለት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ምን መማር እንደሚያስደስተው እንዲጽና እንዲስል ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ስለ ምን እንደጻፍክና እንደሳልክ ንገረኝ!** ብለው ይጠይቁት።



©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 16

## ማንበብና መጻፍ፡ የዚህን መሳሪያ ስም ንገረኝ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ <u>መሳሪያዎች</u>፣ ወይም እውነተኛ መሳሪያዎች**




- ለልጅዎ **እስከ አሁን ስለ መሳሪያዎች ተምረናል። የመሳሪያ ስዕል አሳይሀለሁ። አንተ ደግሞ ስሙን ትነግረኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- የመሳሪያዎች ስዕሎች ያሳዩት። ልጅዎ የመሳሪያውን ስም ባያውቀውም ምንም ማለት አይደለም። የመሳሪያውን ስም እና ለምን እንደሚያገለግል ይንገሩት። በቤትዎ ውስጥ መሳሪያዎች ካሉዎ ልጅዎን እነዚህን እውነተኛ መሳሪያዎች ያሳዩት።
- ስዕሎቹን ነገ ለሚሰራ ስራ ያስቀምጧቸው።

## ያንብቡ፡ *የቅርጽ መስሪያዎች*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ *<u>ቅርጽ መስሪያዎች</u>*፣ ክር ወይም የሀር ክር፣ መቀሶች**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ *የቅርጽ መስሪያዎች* ያንብቡ።
- ካነበባችሁ በኋላ ከመጽሀፍ ላይ ቅርጾችን ተመልከቱ እና በአንድ ክር (ክብ) መስራት ስለምትችሏቸው የተለያዩ ቅርጾች ተነጋገሩ። **ከእነዚህ ቅርጾች ውስጥ የትኞቹን በክር መስራት እንችላለን? እስኪ እንሞክር** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም ክር 3 ቦታ ይቁረጡና ልጅዎን የተለየ ቅርጽ (ሶስት ማዕዘን) እንዲሰራ ያበረታቱት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።




መጋዝ




ካቻ ብቴ



መዶሻ



መፍቻ


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: ሰማይ ጠቀስ ህንጻ መሳል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ እርሳስ ወይም ከለሮች፣ ሰማይ ጠቀስ ህንጻ**

- ለልጅዎ **አሁን ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ትስላለህ። ሰማይ ጠቀስ ህንጻ በሰማይ ላይ ህንጻዎች የሚሰሩት ቅርጽ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የሰማይ ጠቀስ ህንጻ ስእል ተመልከቱና ልጅዎ ምን እንዳየ በተመለከተ ተነጋገሩ።
- **በመጀመሪያ ንድፍ ወይም ፕላን ስራ። በሌላ ቀን በመጫወቻ ሊጥ ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ትሰራለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የሰማይ ጠቀስ ህንጻ ስዕል እንዲሰራ ያድርጉ። ስዕሉን ለቀን 19 ህንጻ መስሪያ ያስቀምጡት።





## በግል መማር: የግንባታ ተሽከርካሪዬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች፣** ***በአማራጭነት - ማጣበቂያ፣ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ለህንጻ መስሪያ የሚያገለግሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ምሳ: አነስተኛ የፕላስቲክ መያዣዎች***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ የግንባታ ተሽከርካሪዎች ተነጋገሩ።
- ከዚያም **የግንባታ ተሽከርቸካሪ መስራት ብትችል ይህ ምን ሊመስል ይችላል? ለምን ያገለግላል?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የተሽከርካሪውን ዲዛይን እንዲያዘጋጅና እንዲስል ያድርጉ። በተጨማሪም ለተሽከርካሪው ሞዴል ሊሰራ ይችላል።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ተሽከርካሪህ ንገረኝ! ምን ተብሎ ይጠራል? ለምን ያገለግላል?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 17

## ማንበብና መጻፍ፡ ምን መሳሪያ ትጠቀማለህ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከቀን 16 የተወሰዱ** **መሳሪያዎች**




- ለልጅዎ **አንድ ድርጊት እጠራለሁ። አንተ ደግሞ ይህን ተግባር ለመስራት ምን መሳሪያ እንደምትጠቀም ትነግረኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ፍንጭ ይስጡት።**… ለመስራት ምን መሳሪያ ትጠቀማለህ?**
  - **እንጨት ለመቁረጥ?** (መጋዝ)
  - **ብሎንና ማሰሪያ ለማጥበቅ?** (ጉጠት)
  - **ብሎን ለማላላት?** (ብሎን መፍቻ)

## የጆርናል ሙከራ: የመሳሪያዎች አገልግሎት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለሮች፣ የመሳሪየያዎች አገልግሎት የጆርናል ገጽ**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ሰዎች መሳሪያዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ሰዎች መሳሪያዎችን እንዴት እንዲጠቀሙባቸው እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **ስለ ጽሁፍህ ልትነግረኝ ትችላለህ? ሰዎች መሳሪያዎችን ለምን ይጠቀማሉ?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:________________

ሰዎች መሳሪያዎችን የሚጠቀሙት ለምንድን ነው?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ




## **STEM:** እስከ 3 መቁጠር

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው እንዴት ጣቶችን በመጠቀም እስከ 3 መቁጠር እንደሚቻል ይለማመዱ። **እስኪ በጣቶቻችን መቁጠር እንለማመድ** ብለው ይንገሩት። በመጀመሪያ እርስዎ ያሳዩት እና **ይህ ምን እንደሆነ ታስታውሳለህ? ምንም ጣቶች አለማንሳት ማለት ዜሮ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ሌሎቹን ደረጃዎች በጋራ ሆናችሁ አጥኑ:
  - **1 -** አውራ ጣትዎን ያንሱ
  - **2 -** አውራ ጣትዎንና ጠቋሚ ጣትዎን ያንሱ
  - **3 -** ሶስቱን የመሀከል ጣቶችዎን ያንሱ
- **አሁን በራስህ እስከ 3 ትቆጥራለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን እራሱን ችሎ ጣቶቹን በመጠቀም እስከ 3 እንዲቆጥር ያድርጉ።

## በግል መማር**:** ቅርጾች መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: የመጫወቻ ሊጥ፣ [ውርጾች](#) ከሳምንት 1 ቀን 3 ወደ ካርዶች ቆርጦ ማውጣት፣ [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ሊጥ](#)**



የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የቅርጾችን ስም ያጥኑ እንዲሁም ጎኖቻቸውን ቁጠሩ።
- ለልጅዎ **እስኪ ቅርጾችን ለመስራት የመጫወቻ ሊጥ እንጠቀም!** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም ከ2-3 ቅርጾች እንዲሰራ ያድርጉ።
- የመጫወቻ ሊጡን ነገ ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ለመስራት ያስቀምጡት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 18

## ማንበብና መጻፍ: 1, 2, ጫማዬን ማሰር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** 1, 2, ጫማዬን ማሰር

- ምት ያላቸው ቃላትን ይለማመዱ። ለልጅዎ **ምት ያላቸው ቃላት መጨረሻቸው በአንድ አይነት ድምጽ የበቃል: net** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **pet። እስኪ ግጥም እናንብብ እና ምት ያላቸው ቃላትን እናዳምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ግጥም ያንብቡ። **መጨረሻቸው አንድ አይነት ድምጽ የሆኑ ቃላትን ሰምቻለሁ: shoe** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **two** ብለው ይንገሩት።
- ግጥሙን በዝግታ ደግማችሁ አንብቡ። ከዚያም **ምን ምት ያላቸው ቃላትን ትሰማለህ?** (two-shoe, four-door, six-sticks, eight-straight, ten-again) ብለው ይጠይቁት።




## ያንብቡ፡ *ቅርጽ መስሪያዎች*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** *ቅርጽ መስሪያዎች፣* **ሁለት ቦታ የተቆራረጠ ወረቀት እና ሁለት አጭር ክሮች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *ቅርጽ መስሪያዎችን* ያንብቡ።
- ከዚያም **የወረቀት ቁርጥራጮች ምን አይነት ቅርጾች እንደሰሩ ታስታውሳለህ? እስኪ አንድ ላይ ለመስራት እንሞክር** ብለው ይንገሩት። ገጽ 16-19ን ይመልከቱና ቁራጭ ወረቀት በመጠቀም በጋራ አራት ማዕዘን ስሩ።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 18

## እስኪ እንንቀሳቀስ: እንቅስቃሴዎች ምን ስሜት እንደሚፈጥሩልኝ

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተወሰኑ ስሜቶች እና እነዚህ ምን አይነት ስሜት እንደሚፈጥሩባችሁ ተነጋገሩ።
- ከዚያም **እስኪ የተለያዩ ስሜቶች የሚፈጥሩ ዳንስ እና እንቅስቃሴዎች እንስራ። ደስተኛ ስንሆን ምን አይነት እንቅስቃሴ እናሳያለን?** ብለው ይጠይቁት።
- የተለያዩ ስሜቶችን ይጥሩና ስሜትዎን ለማሳየት ይደንሱ ወይም ይንቀሳቀሱ።
- ሚና ተቀያየሩ። ልጅዎን ስሜቶች እንዲጠራ፣ እንዲደንስ ወይም እንዲንቀሳቀስ ያድርጉ።
- የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ስሩ። ልጅዎ የሚያየውን ስሜት ሊገምት ይችላል።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር: የቤተሰብ ምሽግ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ጨርቆች፣ ትራሶች፣ ወንበሮች፣ መደገፊያ ያሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**

- ለልጅዎ **እስኪ በጋራ የምንቀመጥበት የቤተሰብ ምሽግ ወይም ድንኳን እንስራ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከታብሌት፣ ስልክ ወይም መጽሀፍ ላይ በቤት ውስጥ የሚሰሩ ምሽጎች ወይም ድንኳኖች ስዕሎች ተመልከቱ።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው የምሽግ ፕላን አዘጋጅተው ይገንቡ።በ2 የተራራቁ ወንበሮች ላይ ጨርቅ በማልበስ ከስር የሚቀመጡበት ምሽግ መስራት ይችላሉ ወይም በሌሎች ቁሶች ትልቅ ምሽግ መስራት ይችላሉ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማገሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።







©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# 1,2, በክል ማይ ሹዝ


ዋን፣ ቱ፣ በክል ማይ ሹዝ።





ስሪ፣ ፎር፣ ሸት ዘ ዶር።

ፋይቭ፣ሲክስ፣ ፒክ አፕ ስቲክስ።



ሰቨን፣ ኤይት፣ ሌይ ዘም ስትሬት።

ናይን፣ ቴን፣ ቢጊን አጌን።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 19

## STEM: ሰማይ ጠቀስ ህንጻ መስራት/መቅረጽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ሰማይ ጠቀስ ህንጻ፣ በቀን 17 የተሰራ የሰማይ ጠቀስ ህንጻ ስዕል፣ የመጫወቻ ሊጥ፣ በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ**



የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።

- ለልጅዎ **ማክሰኞ እለት የሰማይ ጠቀስ ህንጻ ስዕል ስለህል። ዛሬ ደግሞ የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም ሰማይ ጠቀስ ህንጻ ትሰራለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስዕሉን ይመልከቱና በቅርጹ ላይ ስለተጠቀማቸው ነገሮች ይወያዩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም ሰማይ ጠቀስ ህንጻ እንዲሰራ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ሰማይ ጠቀስ ህንጻህ ንገረኝ** ይበሉት።

## በግል መማር፡ የግንባታ ታሪኬ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ከለሮች ወይም እርሳሶች**

- ለልጅዎ **በግንባታ ቦታ ላይ ስለመሆን የተመለከተ ታሪክ መጻፍ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ በግንባታ ቦታ ላይ ስለመሆን የተመለከተ ታሪክ እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ታሪኩን እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ታሪክህ ንገረኝ!** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# ሃሙስ

PK3 **ክፍል** 3 **ሳምንት** 4 **ቀን** 19


## ማንበብና መጻፍ: እኔንም ተከተለኝ

- ለልጅዎ **እስኪ እኔን ተከተለኝ ጨዋታ እንጫወት። እኔ የምልህን አዳምጥና አድርግ!** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ እንደ መቆፈር፣ ሚስማር በመዶሻ መምታት ማስመሰል፣ እንጨት በመጋዝ መቁረጥ ማስመሰል የመሳሰሉ ባለ አንድ ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት።
- ልጅዎ ለእርስዎ መመሪያ መስጠት እንዲችል ሚና ተቀያየሩ።

## የጆርናል ሙከራ: የግንባታ እቃዎች

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከለሮች፣ የግንባታ እቃዎች የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ አይነት የግንባታ እቃዎች ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለመረጠው የግንባታ እቃ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **የመረጥከው የትኛውን የግንባታ እቃ ነው? ይህን እቃ ለምን መረጥከው?** ብለው ይጠይቁት።


ስም:_______________

ከማንኛውም ቁሳቁስ ተጠቅመህ ህንፃ መስራት ብትሽል ምን ትመርጣለህ?


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።






©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ስም:_________________

ከማንኛውም ቁሳቁስ ተጠቅመህ ህንፃ መስራት ብትሽል ምን ትመርጣለህ?

# አርብ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: ቁጥር ማደን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ከ 1-3 ምድብ የቤት ውስጥ እቃዎች፣ ምሳ: 2 ከለሮች፣ 3 አሻንጉሊቶች**

- በክፍል ውስጥ የተለያዩ ምድቦች ያላቸው እቃዎችን ይደብቁ።
- ለልጅዎ **በክፍል ውስጥ እቃዎች ደብቄያለሁ። ፍንጭ እሰጥሀለሁ። ፈልገህ ታገኛቸው እንደሆነ አያለሁ!** ይበሉት። ለልጅዎ እቃዎቹን ፈልጎ እንዲያገኝ ፍንጭ ይስጡት። ለምሳሌ: **ወንበሩ አጠገብ በቀለም የምትለያቸው ሁለት ነገሮች ደብቄያለሁ።**
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ያገኛቸውን ነገሮች እንዲቆጥር ያድርጉ፤ ምሳ: **1፣ 2። ሁለት አሻንጉሊቶች።**
- ልጅዎን እርስዎ ፈልገው የሚቆጥሯው ነገሮች እንዲደብቅ ያድርጉ!

## በግል መማር: ስለ ህንጻ መሰናበት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች: ወረቀት፣ ከለሮች**

- ለልጅዎ **እስከ አሁን ድረስ ስለ ህንጻ ስንማር ቆይተናል** ብለው ይንገሩት። ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ከህንጻ ትምህርቱ ላይ ስለወደደው ነገር ይነጋገሩ። የወደድከው ተግባር ወይም መጽሀፍ አለ? ብለው ይጠይቁት።
- ልዎን ከዚህ ክፍል ውስጥ የወደደውን ክፍል እራሱን ችሎ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለ ምን እንደጻፍክ ንገረኝ። ይህ ለምን ምርጫህ ሆነ?** ብለው ይጠይቁት።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

# አርብ

PK3 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን 20

## ማንበብና መጻፍ፡ ስለ ተግባሮቼ መግለጽ

- ልጅዎን **እስኪ ጌም እንጫወት። አሁን የተወሰነ ነገር እሰራለሁ። አንተ ደግሞ ስለምሰራው ነገር ትገልጽልኛለህ ወይም ትነግረኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎ በቀላሉ ሊገልጸው የሚችል ተግባር ይስሩ። እየቆፈሩ፣ እየቆረጡ፣ እየደነሱ፣ እየገነቡ፣ ወዘተ ማስመሰል።
- ሚና ተቀያየሩ። ልጅዎን እርስዎ የሚገልጹት ተግባር እንዲሰራ ያድርጉ።

## ያንብቡ፡ ቅርጽ መስሪያዎች


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ *ቅርጽ መስሪያዎች*፣ 5 ከለሮች፣ ስንጥሮች ወይም የጥጥ መወልወያዎች**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ *ቅርጽ መስሪያዎች* ያንብቡ።
- ከዚያም **በ 5 ስንጥሮች የትኛው ቅርጽ ይሰራል? እስኪ አንድ ላይ ሆነን እንስራ** ብለው ይንገሩት። ከገጽ 20-23 ተመልከቱና ከለሮች፣ ስንጥሮች፣ ወይም የጥጥ መወልወያዎች በመጠቀም ባለ አምስት ማእዘን ቅርጽ ይስሩ።


©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።

ክፍል 3 ስለ ህንጻና ግንባታ የተመለከተ ነው! ህጻናት ከፕላንና ረቂቅ ንድፎች ዝግጅት ጀምረው እነዚህን ወደ ህንጻ እስከመቀየር ድረስ ስለ ግንባታ ሂደት ይማራሉ።



AppleTree
©2020. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ ይሆናል።